# ጥምቀት በተዋሕዶ፤

ሐዋርያዊት ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአምላክ መለኮታዊ ዘላለማዊ ሀልዎቱን ለመረዳት እንዲሁ ነጠላ ጥሬ ቃሉን በስሜት ብልጭታና በማንኪያ ጠብታ በብልጣብልጥነትና በጮሌነት ቆንጽሎ ፈጥኖ በመሮጥና በመሽቀዳደም ወይንም መስሎ በመታየት ላይ የተመሠረተ መሆን  እንደሌለበት ሊቃውንት  አባቶቻችን አጥብቀው ያስጠነቅቃሉ ። ይልቁንም ምጡቅና ጥልቅ ሃይማኖታዊ አስተምህሮቱን ጠብቆ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ትንቢት በሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ኩነትና ተፈጻሚነት እንዲሁም በሊቃውንት ትርጓሜ አንድምታ አብራሪነት አያይዞ፣ አመሳክሮና **አዋሕዶ** ጠይቆ የማወቅ የመረዳትና የማመን ከመነሻ እስከ መድረሻ መሠረታዊ ጥንካሬና ብቃት ያለው ዕውቀትን የሚጠይቅ ቀጥተኛ ሃይማኖታዊ ትምህርት መሆኑን መረዳት ግድ የሚል መሆኑን አበክረው ይመክራሉ ።

የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት ስናስብ **መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን** አስቀድሞ ማን እንደሆነ ማወቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ሃይማኖታዊ የትምህርት ገጽታ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ የአብርሃም፣ የይሳቅ፣ ያዕቆብ፣ የዳዊት፣ የሰለሞን..  አይሁዳዊ ዘር ከብሉይ ኪዳን ቅዱስ ካህን ከአባቱ ዘካሪያስ እና ከእናቱ ቅድስት ኤልሳቤጥ በዘመነ አረጋዊነታቸው በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ከኢየሱስ ክርስቶስ ስደስት ወራት በፊት አስቀደሞ የተጸነሰ ነው።/ **ሉቃስ 1፤5-15 /** ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሥጋ ያለአባት አይሁዳዊ የዘር ሐረግ ካላት ከተመረጠች ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም አምላክ ሰውን መስሎ መወለዱ፤ ዮሐንስም ከቅድስት ኤልሳቤጥና ከካህኑ ዘካርያስ በቅዱስ ጋብቻ በፍህቶተ ሥጋ በመወለዱ በአይሁዳዊ ትውልድ ሐረጋቸው የሥጋ ዝምድና አላቸው **/ሉቅስ 1፤39/**

**ወአንተኒ ሕጻን ነብየ ልዑል ትሰመይ** መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ሕጻን ገና በማኅጸን እያለ ለፈጣሪው ከአምልኮት ስግደቱ አስቀድሞ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት የሚሰብክ የሚያስተምር መሆኑ ትንቢት የተነገረለት **ጎድጓዳውና ሸለቆው ይሙላ፤ ተራራውና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይበል፤ ሸካራው ይለስልስ፤ ጠማው ይቅና ፤/ሲሳያስ 40፤3/  በብሉይ ኪዳን መጨረሻ ዘመን የተወለደ፤ በሐዲስ ኪዳን ከእኔ በኃላ የሚመጣው ከእኔ ይበልጣል፤ ከእኔ በፊትም  አስቀድሞ ነበር። /ዮሐንስ 1፤15/** እያለ በማስተማሩና በማወጁ የመጨረሻው ነቢይ **ተፍጻሜተ ነቢያት** ሲሆን፤ የክርስቶስን መወለድ ከማኅጸን ሳለ ጀምሮ ለፈጣሪው መስገዱ ቀጥሎም ተዘዋውሮ በማስተማሩንና በኋላም ማጥመቁን አጠቃሎ የሐዲስ ኪዳን የመጀመሪያው ሐዋርያ/ **ቀዳሜ ሐዋርያት** ነው።

ሊቃውንት ሁለቱን በማጣጣም **ተፈጻሜተ ነቢያት ቀዳሜ ሐዋርያት መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ** ብለው ሲጠሩት፤ ለአይሁዳዊ ቅዱሳን እናት እና አባቱ በስተሽምግልና የመጀመሪያም የመጨረሻም በመሆን በመወለዱ የብሉይ ኪዳን መጠናቀቂያ የሐዲስ ኪዳን ዘመን መጀመሪያ ወይም መሸጋገሪያ መሆኑን ከማብራራቱም በተጨማሪ፤ አሮጌው ዘመን በአዲስ መተካት የዘመናት ተፈጥሮአዊ የማያቋርጥ ዑደት መሆኑን አስተምሮናል ማለት ነው። ዮሐንስ የሚለው ስም ለመጀመሪያ ጊዜ መጠሪያ ሆኖ ታወቀ ስሙን በመጥራቱ ብቻ በልደቱ መጀመሪያ አባቱ ዘካሪያስ አንደበቱ ተይዞ ምላሱ ታጥፎ ነበርና ስሙን ዮሐንስ ብሎ ሲጠራ ርዕቱ እንዲሆን ታአምር አደረገ። **/ሉቃስ 1፤64/** ቅዱስ ዮሐንስ ከወላጅ ዘመዱ ፈልሶ በገዳም ድንጋይ ተንተርሶ፣ ድምጸ አራዊቱን ግርማ ሌሊቱን ታግሶ፣ ቆዳ ለብሶ የበረሐ ማር ልሶ፣ በጾም በጸሎት ተመላልሶ በብቸኝነት በመኖር ርዕሰ ባህታዊ መናኝ  የሰላም ሰው ንብረቱ ከዳም የሆነ ነብይ በመባል አደገ። **/ማቴዎስ 3፤4/**  ቅዱስ ያሬድ **ዩሐንስ ክቡር  ነብየ  ልዑል  ብዕሴ  ሰላም ዘንብረቱ ገዳም** ብሎ እንደዘመረ። መጽሐፍ ቅዱስ  የመጥምቀ መለኮት ዮሐንስን ቅድስና ሲያስረዳን **በምድር ላይ ከናቶች ከተወለዱት መካከል እንደ ዮሐንስ ያለ ማንም የለም** ሲል አስተዋውቆናል። **/ሉቃስ 7፤28/**

በመሆኑም ሙሉ ቅድስናውን እንደያዘ ቅሩብ መለኮት ሆኖ ሰማይና ምድርን፣ ጨለማውንና ብርሃኑን፣ የማይታይና የሚታየወን፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀሰውን፣ የብሱና ውቅያኖሱን፣ እንስሳቱና አራዊቱን **«ሁን!»** በማለት ብቻ የፈጠረውን አምላክ፤ በተለይም የሰውን ልጅ አፈሩን፣ ውሃውንና እስትንፋሱን **አዋሕዶ** በአምሳሉና በምሳሌው አሳምሮና አብልጦ የፍጥረታት ሁሉ ገዥ እንዲሆን ያነጻውን፤ ቅድመ ዓለም ያለእናት ቃል የነበረ፣ ከዓለም በኋላ ከእናት ያለአባት **ቃል ሥጋ ሆኖ መንፈስ ቅዱስ ተዋሕዶ** የተገለጠውን አልፋና ዖሜጋ የሆነውን ፈጣሪውን ለማጥመቅ ቅዱስ ዮሐንስ ከእናቱ ማኅጸን ጀምሮ ተመረጠ። **ቀደስኩከ ምከርሰ እምከ/ ገና ከእናትህ መሐጸን ሳለህ መረጥኩህ** ተብሎ እንደተጻፈ።

ጥምቀት በመለኮታዊ ትርጉሙ መወለድ **በተዋሕዶ** መገለጥ ወይም መታየት ሲሆን፤ በንስሐ ሰጭነቱ ደግሞ መንጻት፣ መዳን ነው። በመሆኑም ቅዱስ ዮሐንስ በገሊላና በዮርዳኖስ እስከ ክርስቶስ መጠመቅ ድረስ  ያደረገው ጥምቀት በሙሉ የንስሐ የውሃ ጥምቀት ነው። **እነሆ እኔ ለንስሐ በውሃ አጠምቃች ኋለሁ ነገርግን  ከእኔ በኋላ የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል። /ማቴዎስ 3፤11/** ጌታችን መድኅኒታችን ኢሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወርዶ በዮሐንስ እጅ በባህረ ዮርዳኖስ ለመጠመቅ ሄደ። **ማቴዎስ/3፤13/ ቅዱስ ያሬድ ሆረ ኢየሱስ እምገሊላ ሐበ ዮሐንስ ከመያጠምቆ በፈለገ ዮርዳኖስ** ብሎ ቃኝቶ እንደዘመረ።

ቅኝቱ የሚያመለክተው ገሊላ ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን፤ ዮርዳኖስ ደግሞ በስተደቡብ በኩል ይገኛል። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰሜንኛው ክፍል ወደ ደቡብ ክፍል ከላይ ወደ ታች ጉዞ አድርጎ መጠመቁን የሚገልጽ ግሥ ሲሆን፤ የገሊላ ባህር ከላይ ከሰሜነኛው ወደታችኛው ወደ ደቡብ ቀጥ ብሎ እየወረደ ሲመጣ ዮርዳኖስ ወንዝ ይሆናል፤ እረቂቅ መለኮታዊ ትርጉሙ **ቀደሞ ከዓለም በፊት ያለእናት የነበረ  ወደታች ወደ መሬት ወርዶ ከድንግል በሥጋ  ተወለዶ  ተጠመቀ** ሚለውን የሚያብራራ ሲሆን፤

**ወረደ ወልድ እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት** የሚለውን ቅኝት ጋር አዛምዶ ብሉያቱን እና ሐዲሳቱን አገናኝቶ **አዋሕዶ** ቦታውንም እራሱ ስለመረጠውና ስለቀደሰው የኢየሩሳሌም ከተሞች የባህረ ገሊላንና ዮርዳኖስን ወንዝ ከላይ ወደታች መልካ ምድራዊ አቀማመጥ ጋር አገናዝቦ አስተምሮናል ማለት ነው ፡፡

ከዚያም ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ከመጣ በኋላ ዮሐንስ በነገሩ ተስማምቶ **ኢየሱስን አጠመቀው እየሱስም ተጠመቀ /ማቴዎስ 3፤16/** ቅዱስ ያሬድ **ተጠምቀ ሰማያዊ በዕደ መሬታዊ ፡፡** አምላክ ምድራዊ ባህሪ ባለው በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ፤ ይህም ከላይ እንደ ተጠቀሰው ቅዱስ ዮሐንስ ዘመነ ብሉይ ሲጠናቀቅ ለዘመነ ሐዲስ አሸጋጋሪ፣ መንገድ ጠራጊና አዋጅ ነጋሪ ሆኖ ከቆየ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስን አጥመቀ፤ ኢየሱስ ክርስቶስም ዘመነ ፍዳን አጠናቆ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመንን ከተፈጸመ በሰላሳ የዓመተ ምሕረት ዘመኑ አዲስ ኪዳን አጽንቶ በዮንሐንስ እጅ መጠመቁን ያስረዳናል ማለት ነው፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በባህረ ዮርዳኖስ መገግኘት **ወልድ፣** ሲሆን ሰማይ ተከፍቶ  በእርግብ አምሳል ሲውጣና ሲወርድ ታየ **መንፈስ ቅዱስ፣ ዝንቱ ውዕቱ ወልድየ ዘአፈቅር፡፡** በእረሱ ደስ የሚለኝ የማፈቅረው ልጀ ይህ ነው የሚለው ድምጽ ከሰማይ ተሰማ **አብ፣ /ማቴዎስ 3፤16/** ሦስቱም **በተዋሕዶ**  በማይመረመር ቅጽበታዊ ሁኔታ በባህረ ዮርዳኖስ አንድ አምላክ ተገለጠ ይህም **አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ** አምላክ የሚለውን ምስጢረ ጥምቀት **በተዋሕዶ** ምስጢረ ሥላሴን  ተገልጾ አስተምሮ አሳምኖናል ማለት ነው፡፡  **ቅዱስ ያሬድም አዲኀ ተስአ ወተስአተ ነገደ ቆመ እማዕከለ ባህር ወወጻ በሰላም፡፡** አምላክ ወደ ባህር ገብቶ ቆመ ተጠምቆ በሰላም ወጣ በማለት ዘመረ አመሰገነ፡፡

ከላይ ከረጅሙ በአጭሩ ከሰፊው በጠባቡ የተጠቀሰው መንፈሳዊ መለኮታዊ አስተምህሮ እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ የጌታችን መደኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት በማሰብ ለሁለት ሺህ ስምንት ዓመታት እያከበረች ነው፡፡ የበዓሉ አከባበር ዝርዝር  የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን አንድነት እንዲሁም የሊቃውንት አስተምህሮ **በተዋሕዶ** እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የበዓሉ የሚከበረው በየዓመቱ ጥር 10 እና ጥር 11 በመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን ይከናወናል፡፡  በተመሳሳይ ስዓት የደወል ድምጽ ተሰምቶ በመላ ካህናቱ ሥርዓቱ ተጠብቆ ዋዜማ ይቆማል፤ ከዚያም ጌታ በሲና ተራራ ለመሴ የሰጠው **ጽላተ ተእዛዛተ ሕግ** ሙሉ ለሙሉ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በሐዲስ ኪዳን **አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ፡፡ አነ ውዕቱ ቀዳማዊ  ወዘድሐራዊ/** የመጨረሻውም የመጀመሪያውም እኔ ነኝ፡፡ **/ራዕይ 1፤8/** የሚለው **ወልደ አምላክ ትእዛዝ  ወልደ ማርያም መንፈስ ቅዱስ ቃለ ወንጌል  በተዋሕዶ የአንድ የአምላክ ቃል** ያለበት **ታቦታተ ሕግ** ከመንበረ ክብሩ ወጥቶ ጉዞ ወደ ባህረ ጥምቀቱ ይሆናል፤ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ተነስቶ ወደ ዮርዳኖስ ያደረገውን ጉዞ ያስተምረናል፡፡ ቅዱስ ያሬድ **ሆረ ኢየሱስ እምገሊላ  ሐበ  ዮሐንስ  ከመያጥምቆ  በፈለገ  ዮርዳኖስ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሄደ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ያጠምቀው ዘንድ፡፡ ወረደ ወልድ እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት** ወልድ ኢሱስ ክርስቶስ ከሰማይ የወረደው ለመጠመቅ መጣ/ሄደ የሚለው ጣዕመ ዝማሬ እየተሰማ ታቦታተ ሕጉ በባህረ ጥምቀቱ ቦታ ይደርሳል፡፡

ለሊቱን በሙሉ ካህናት እንደ መላእክት ለፈጣሪያቸው የሚገባውን ዝማሬ ያሰማሉ ሲነጋም ቅዳሴ ይቀደሳል፤ ኪዚያም ታቦታተ ሕጉ በቆመበት አራቱም ወንጌላውያን የኢየሱስ ክርስቶስ መጠመቅ አስመልክቶ የዘገቡት/ የጻፉት በአራቱም ማዕዘን ይነበባል፡፡ ሙሉ ጸሎት ተደርሶ ባህረ ጥምቀቱ **በስመ አብ ወወልድ ወመንፈ ቅዱስ አሐዱ አምላክ** ተባርኮ ለካህናቱ ለማኅበረ ምዕመናኑ ይረጫል፡፡ **ተጠምቀ ሰማያዊ  በዕደ መሬታዊ** ፤ ሰማያዊ አምላክ በምድራዊ ሰው ተጠመቀ፤ **ሐዲኀ ተስአ ወተስአተ ነገደ ገባ ቆመ በማዕከለ ባህር ወወጻ በሰላም**  አምላክ ወደ ባህር ገብቶ ቆመ ተጠምቆ በሰላም ወጣ፡፡ የሚሉት ጣዕመ ዜማ ጥልቀት ባለው መንፈሳዊ ስሜት መዝሙር ታጅቦ የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ማደርያ ታቦታተ ሕጉ በክብር ወደ መንበረ ክብሩ ይመለሳል፡፡

በዚህ ወር፣ በዚህ  ስዓት፣ በዚህ ደቂቃ፤ ሁለት ሺህ ስምንት ዓመታት ወደኋላ ተጉዘን ቅድመ ዓለም የነበረ አምላክ ቃል፤ ዓለምን አሳልፎ ቃል ሥጋ ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው፤ የዓለም ገዥ የዓለም ፈጣሪ አምላክ፤ እኛን የሰውን ልጅ በአምሳሉ የፈጠረና የፍጥረታት ሁሉ ገዥ ያደረገን፤ የሰው ልጅ ሕግን በመተላለፍ ከተፈረደበት የሞት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ተጥሎ እንዳይቀር የፈጠረውን ብልህ ፍጥረት ለመፈለግ **ወረደ ተወለደ ተጠመቀ፤ በጥምቀቱ  የመንፈስ ቅዱስ ልጅነት እናገኝ  ዘንድ ዳግም  ወለደን፤ ከሞት በኋላ ሕይወት በንስሐ አሸጋግሮ  የመንግስተ ዘማያትን በር ከፍቶ የቅድስናው በረከት ተካፋዮች የርስቱ ውራሾች  እንድንሆን  አምላክ  በአጭር  ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ  የሥጋ  ዘመዱ  በሆነ መናኝ  ቅዱስ ዮሐንስ እጅ መጠመቁን** እያሰብን በጥንታዊት ሐዋርያዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ እንደዘገበው አባቶቻችን ሊቃውንት **በተዋሕዶ** እንዳስተማሩት እዚህ በስደት በምንኖርበት በእንግሊዝ ሀገር ሁለት ሺህ ስምንተኛውን የጌታችን የአምላካችን የመደኀኒታችን ኢየሱስ ከርስቶስ በዓለ ጥምቀት በአንድነት ዛሬ ጥር 2008 ዓ.ም አክብረናል፡፡

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!**

**መጋቤ ጥበብ መንገሻ መልኬ**

**የሰሜን ምዕራብ  አውሮፓ ሀገረ ስብከት ዋና ጽሐፊ**

**ጥር 2008 ዓ.ም፤ ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ፤ በታላቋ ብርታንያ፤ ለንደን፤**